# ኢህአዴግ ብቻውን የማይወጣው ተግዳሮት

## ----“እኛስ ምን አይነት ብሄራዊ የአላማ አንድነት እያቀረብን ነው?”

**አክሎግ ቢራራ (ዶር)**

እኔ የኢትዮጵያ ባለ ውለታ ነኝ የሚል የጸና እምነት አለኝ። ይህን ስል ወላጆቸ፤ አያቶቸና ቅድመ አያቶቸ የተለየ ጥቅም አግኝተዋል ማለቴ አይደለም። ይህች አገር የማንነቴ መገለጫ ናት ማለቴ ነው። ሕብረ ብሄር በሆነ አገር፤ ዜጎች ከተለያዩ ብሄሮች፤ ዘሮችና ኃይማኖቶች ሊመጡ ይችላሉ። ይህ የተፈጥሮ ጸጋና መብት ሲሆን ለመለያየት መሰረት መሆን የለበትም። ከብሄርና ከኃይማኖት ባሻገር፤ ሰብሳቢ መለያቸው ግን የአንድ አገር ዜጋ መሆናቸው ነው። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ አሜሪካ ነው። ከሁሉም አገሮች የተሰበሰቡ ብሄሮች፤ የኃይማኖት ተከታዮች አገር ናት አሜሪካ። ሆኖም፤ አንድ ግለሰብ ዜግነትህ/ዜግነትሽ ከየት ነው ቢባል/ብትባል አሜሪካዊ እንጅ ጀረመናዊ ወይንም እንግሊዛዊ ወይንም ናይጀሪያዊ አይልም/አትልም። የእኛም አገር ሁኔታ ከዚህ የተለየ አይደለም። ብሄራችን፤ ኃይማኖታችን፤ መደባችን፤ አመለካከታችን ወዘተርፈ ይለያያል። ይህ ችግር አይደለም፤ እንዲያውም ጸጋ ነው። ወደ አሜሪካ ተሰደን ዜግነት ስንጠይቅ የእኔን “አማራነት፤ ትግሬነት፤ ኦሮሞነት ወዘተርፈ” ፓስፖርቴ ላይ ለጥፉልኝ ብንል እብድ እንባላለን፤ ወደመጣህበት/ወደመጣሽበት! ሳንባልም አንቀርም። ይህን አስቡት። አሜሪካዊ ለመሆን ብሄራችን የመታወቂያ መለያችን አይሆንም። ያሳደገችን ኢትዮጵያ ስትሆን ግን “እኔ መለያየ ዐማራ፤ ኦሮሞ” ወዘተርፈ እያልን እንስተጋባለን። ይህ የመለያ መርህ ለአገራችን ጥፋት ግብዐት ሆኗል። የሕዝቡን አመጽ ስኬታማ ለማድረግ አንዱ የሚጎትተን ይህ ይሆናል የሚል ግምት አለኝ።

በዚህም ምክንያት፤ ወዳጀ የሆኑት፤ ምክራቸው አግባብ ያለው ጋሽ ገብረየስ ቤኛ በኢትዮጵያ የውይይትና መፍትሄ መድረክ የተናገሩትን እጠቅሳለሁ። **<u>“እኛ ኢትዮጵያዊያን ብለን መነሳት ግዴታችን ነው።”</u>** አንድ አገር አለን ካልን “እኛ ኢትዮጵያዊያን” ብለን ለመወያየት መድፈር አለብን። መለስ ዜናዊ ከመቃብሩ ሆኖ የሚያሽከረከረውን የብሄር፤ የቋንቋና የጎጥ ልዩነት መመሪያ አድርገን የትም አንደርስም። በብሄር ትምክህተኛነት ሆነ በጠባብ ብሄርተኝነት ተበክለን የትም አንደርስም። ከፊታችን ላይ ተደቅኖ የሚታየው ሃቅ ባለፉት አስራ ሁለት ወራቶች ብቻ መስዋእት የሆኑት ወጣቶችና የወለዷቸው እናቶች፤ አባቶች፤ እህቶች፤ ወንድሞችና ሌሎች ዘመዶች እነዚህን ወገኖቻችሁን አትርሱ የሚል የማይረሳ መልእክትና መመሪያ ሰጥተውናል። ለቅሷቸው ለቅሷችን ነው እንበል። “እኛ ኢትዮጵያዊያን” የእነዚህን መስዋትነት አንረሳም፤ የምንታገለው ሁሉን የሚያሳትፍ ስርዓት እንዲመሰረት ነው ብንል ይበጃል። ለማፈራረሱ ህወሓቶች ይበቃሉ። የዐማራው፤ የኦሮሞው፤ የአኟኩ፤ የደቡቡና የሌላው ወጣት ትውልድ መስዋእት የሆነው አገሩን ለማፈራረስ አይመስለኝም። መስዋእት የሆኑት ለፍትህ፤ ለእኩልነት፤ ለሕግ የበላይነት፤ ለመልካም አስተዳደር እና ለዚህ ሁሉ በዘላቂነት ለሚያገለግል ለሕዝብ ተገዢና ታዛዢ ለሆነ የዲሞክራሲ ስርዓት አስፈላጊነት ነው።

የአስቸኳይ አዋጁ ከታወጀ ወዲህ በጎንደር፤ በባህር ዳርና በሌሎች የዐማራ ክልል ቦታዎች እጅግ የሚዘገንን እልቂትና አፈና እየተካሄደ ነው። ወጣቱ ትውልድና ገበሪዎች ባላቸው አቅም ሰብአዊ መብታቸውን፤ ማንነታቸውንና ህልውናቸውን ለማስከበር እየታገሉ፤ መስዋእት እየሆኑ ነው። ጨካኙ የህወሓት የጦር ኃይልና ልዩ ቡድን የኮሌጅና የሌላ ከፍተኛ ትምህርት ተሳታፊዎችን በገፍ እያሰረ ነው። በተመሳሳይ፤ ይህ በህወሓት የበላይነት የሚመራ ልዩ ኃይል በኦሮሞያ የሚማሩና የሚያስተምሩ የከፍተኛ ትምህርት አባላትን በገፍ እያሰረ ነው። ባጭሩ፤ የአስቸኳዩ አዋጅ ሁኔታዎችን አባብሷል ለማለት ይቻላል። ግፉ የሚካሄደው በአብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ በተለይ በወጣቱ ትውልድ ላይ ስለሆነ በተቃዋሚው ክፍል የሚገኙ ምሁራን፤ ልሂቃንና የተቃዋሚ ፓርቲዎች ያላቸው ምርጫ አንድ ብቻ ነው። መተባበርና አገሪቱን ከመፈራረስ፤ ሕዝቧን ከእልቂት ማዳን።

የመመጀመሪያው መርህ የኢትዮጵያን ግዛታዊ አንድነት፤ ነጻነት እና ሉዐላዊነት መቀበል ነው። ሌላው ልዩነት ሁሉ በድርድር ሊፈታ ይቻላል። ሁሉም ብሄረሰብ በህወሓቶች እየተበደለ፤ እየተገረፈ፤ እየታሰረ፤ እየተመዘበረ ነው። ህወሓቶች በሰላም ሆነ በሕዝብ አመጽ የሚታገለውን አይምሩም፤ የፕሮፌሰር መረራ ጉዲና መታሰር ለዚህ ዋቢ ነው። ዐማራውና ኦሮሞው ተባብሮ ይህን አፋኝ ቡድን ከስልጣን ማስለቀቅ ወይንም ወደ ድርድር እንዲዞር ማድረግ ግድ ይላል። በአብዛኛው፤ የኢትዮጵያ ችግር የብሄር ልዩነት አይደለም። የህወሓት ጭቆና ነው። “ኢትዮጵያ እስር ቤት ሆናለች” ካልን ሁሉም ኢትዮጵያዊያን እስር ቤት ናቸው ማለት ነው። ስለሆነም፤ ከዚህ እስር ቤት መጥቆ ለመውጣት የሚቻለው የህወሓት ጭቆናና ግፍ መተባበርን፤ አብሮ መስራትን የሚጠይቅ መሆኑን መቀበል ነው።

የማቀርበው ምክር እንዲህ የሚል ነው። **<u>ከፓርቲ አምልኮ</u>** በላይ ለሕዝብ ደህንነት፤ ለሕዝብ ፍትህ፤ ለሕዝብ ክብር፤ ለሕዝብ ነጻነትና እኩልነት፤ ለሕዝብ ስልጣን መረባረብንና መተባበርን እናስቀድም። የቡድን ወይንም የፓርቲ አምልኮ ያስከተለውን

አሉታዊ ውጤት ለማጤን ያለፉት 25 ዓመታት የአፈናና የምዝበራ ታሪካችን ዋቢ ነው። ሕዝብ ከዚህ የባሰ ሊመጣ አይችልም እያለ ነው። እኛስ?

**የማይለያየውን ሕዝብ ማለያየት በታሪክ ያስጠይቃል**

በመሬት ላይ ያለው ሃቅ አንድ ነው። የዐማራው፤ የኦሮሞው፤ የአኟኩ፤ የኦጋዴን ሶማሌው፤ የደቡቡ፤ የአፋሩ፤ የትግራዩ ወዘተርፈ ሕዝብ የገጠመው ችግር በአብዛኛው ተመሳሳይ ነው። ይኼውም፤ የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ መብትና ነጻነት አለመከበሩ ነው። በግልጽ የሚታየው አንድ በአስቸኳይ መፈታት ያለበት ክስተት፤ ስርዓቱን "እንቃወማለን" የሚለው ክፍል በአንድነት፤ ማለትም በኢትዮጵያዊነት ለመነሳት አለመቻሉ ነው። በኢትዮጵያዊነት መነሳት፤ ከብሄር፤ ከመንደር፤ ከቡድን በላይ እናስብ ማለቴ ነው። የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ መብትና ነጻነት የሚከበርባትን ዲሞክራሳዊት ኢትዮጵያ እንመስርት ማለቴ ነው። የጥቂቶችን የፖለቲካና የኢኮኖሚ የበላይነት (Monoploy) አፍርሰን አገር አቀፍ በሆነ ደረጃ የሁሉም ብሄሮች አባላት በዜግነታቸውና በችሎታቸው የሚሳተፉባትን እና ከድህነት ነጻ ወጥቶ የሚኖርባትን ኢትዮጵያ እንመስርት ማለቴ ነው። ኢትዮጵያዊነት የዐማራውንና የኦሮሞውን፤ የአፋሩንና የትግራዩን፤ የአኟኩንና የወላይታውን ሕዝብ ወዘተ ማንነት አይጻረርም፤ እንዲያውም ያጠናክረዋል። ምክንያቱም የጋራ የሆነ የዜግነት መታወቂያውን ይዞ ለጋራ ራእይ፤ ለጋራ ግብ፤ ለጋራ ነጻነትና ሰብአዊ መብት መከበር ይታገላል።

ስለሆነም፤ መሰረታዊ ስርዓት ወለድ ችግሩ እንዳለ ሆኖ፤ በኢትዮጵያዊነታችን የምናምን ሁሉ እርብርባችን በመተባበራችን ዙሪያ ቢሆን ይመረጣል። መተባበራችን ጥንካሬን ይፈጥራል። አሁን የምናደርገው የተበታተነ ወይንም ያልተቀነባበረ ትግል መስዋእት ለሆኑት ወገኖቻችንና ለወላጆቻቸው የሚያኮራ ሆኖ አይታይም። ህወሓቶች እየነጠሉ መግደላቸውንና ማፈናቸውን እንዲቀጥሉ እረድቷቸዋል። መበታተናችን አሁንም እንደገና፤ የለውጥ እድሉ እንዲያመልጠን ግብአት እያደረገ ነው በሚል ትንተናየን እቀጥላለሁ።

በቅንነት ካየነው እና ከሰራን፤ እኛ ኢትዮጵያዊያን ችግሮቻችን በጋራ ተወያይተን ለመፍታት እንችላለን የሚል እምነቴ አሁንም ጠንካራ ነው። ሆኖም፤ **<u>እርግማን ይሁን</u>** ሌላ እድሎች በተደጋጋሚ አምልጠውናል፤ አሁንም እያመለጡን ነው። ምክንያቱም፤ ኢትዮጵያ "በመንታ መንገድ" ትገኛለች ስንል ከአርባ ዓመታት በላይ ሆኖናል። አንዲት አገር "በመንታ መንገድ ላይ ናት እየተባለ" ሲነገርላት የቆየች ብቸኛ አገር ኢትዮጵያ ሳትሆን አትቀርም። በመንታ መንገድ ላይ ስትሽከረከር ከቆየች ማን እዚህ የወደፊት እድሏ አስተማማኝ ካልሆነ ደረጃ ላይ አደረሳት? ለመሆኑ ተቆርቋሪና መካሪ የሆኑ ምሁራንና ልሂቃን አሏት? ተመካሪ የሆኑ፤ ከሌላው ለመማር የሚችሉ፤ አዲስ አገር ወዳድ፤ መላውን ሕዝብ አፍቃሪ የሆኑ ዜጎች አሏት? መቸ ይሆን የመንታ መንገድ ውይይት አቁመን ብሄራዊ ከሆነ **<u>የጋራ (ኢትዮጵያዊ) ዓላማ</u>** ላይ የምንደረሰው? ትችት ብቻውን ለማንም አገር አይጠቅምም። ዛሬ ኢትዮጵያና መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚሾኙት ለጋራ ብሄራዊ ዓላማ መፈላለግን፤ መደጋገፍን፤ መተባበርን፤ መደማመጥን፤ መከባበርን፤ አንዱ ከሌላው መማርን፤ የአንዱን ብሶት ሌላው ማዳመጥን፤ በዲፕሎማሲው በኩል አብሮና ተባብሮ መስራትን፤ መስዋእት እየከፈለ ላለው ትውልድ ያልተቆጠበ ድጋፍ መስጠትን፤ መጠላለፍን አቁሞ በአፋኙና በጨቋኙ ስርዓት ላይ መረባረብን ነው እላለሁ። ይህን ለማድረግ እያንዳንዳችን የኢትዮጵያ እና **<u>የመላው ሕዝቧ የለውጥ አምባሳደር</u>** ሆነን መስራት አለብን! ጊዜ የለንም። በእኔ እድሜ ክልል ያለው ትውልድ ጠቃሚ ስራ ሊሰራ የሚችለው ቢበዛ ለሚቀጥሉት 10 ዓመት ነው። ራሱን መተካት አለበት። ለአገር የማሰብ ልምድ አለው።

የእኔ ትውልድ ከራሱ በላይ ለሃገሩ የሚያስብ ነበር። መለስ ብለን ያደረግነውን ጥሩም፤ መጥፎም ነገር እናስብ። ጥሩውን ለሌሎች እተወዋለሁ፤ ራስን ማመጎስ ስለሚቀፈኝ። ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን አውርደን ደርግን ተካን። ደርግን አስወግደን የአሁኑን ከፋፋይ፤ ጸረ-ኢትዮጵያ፤ ጸረ-ሕዝብ፤ ጸረ-ፍትህ፤ ሙሰኛና መዝባሪ ስርዓት መሰረትን። ይህ ቡድን ከመቸውም የባሰ ነው የሚያስብለው ሕዝቡን በብሄር፤ በቋንቋና በኃይማኖት መከፋፈሉ፤ የአንድ አናሳ ብሄር የበላይነትን ማምለኩ፤ አገርን ለመገነጣጠል አመች የሆነውን **<u>አንቀጽ 39</u>** በሕገ መንግሥቱ አስገብቶ ኢትዮጵያ እንድትከፋፈል ማመቻቸቱ፤ የኢትዮጵያን የባህር በር ማዘጋቱ ጭምር ነው። ከዚህ የባሰ ጸረ-ኢትዮጵያዊነት ያለ አይመስለኝም፤ አገሩን እንድትገነጣጠል ፈቅዶና አመቻችቶ ለአደጋ መዳረግ ብሄራዊ ክህደት ነው። የብሄር ድርጅቶች የሚከተሉት አደገኛ የፖለቲካ አደረጃጀትና የአመራር መንገድ ከዚህ ጸረ-እትዮጵያና ጸረ-ኢትዮጵያዊነት መርህ የመጣ ነው። በህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ የተወለደውና ያደገው ትውልድ ሆነ ተብሎ **<u>ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን</u>** እንዳያውቅ ተደርጓል። እንዲበታተን ተገዷል።

ህወሓት ለጭቁን ብሄሮች ቆሚያለሁ ብሎ መሬታቸውን መንጠቁ፤ ዐማራውን **<u>ጠላት ከማድረጉ</u>** በላይ፤ በጭቁን ብሄሮች ላይ ጦርነት መክፈቱ አንዱ መታወቂያ ነው፤ በተለይ በሰፊው የወጣት ትውልድ ላይ የሚያድርገው የጭካኔ አገዛዝ። የኮንሶንና የኦሞ ሸለቆን ሕዝብ የስቃይ ሁኔታ እና ኃብታም የነበረውን የአፋር ሕዝብ ሁኔታዎች ብቻ ማየቱ ይበቃል። እኔ ኢትዮጵያ ስኖርና ስሰራ የአፋር ለማኝ አይቸ አላውቅም ነበር። የአፋር ክልልል ከራሱ በላይ የሚተርፍ የተፈጥሮ ኃብት

አለው፤ አሁን ህወሓቶች የነጠቁት ማለት ነው። ከብሄር በላይ ብናየው፤ ሰፊውን ወጣት ትውልድ የህወሓት አልሞ ተኳሾች ኢላማና ሰለባ አድርጎ እርጋታ ሊኖር አይችልም። ይህ ስርዓት በአገር ውስጥ የአገዛዝ ሁኔታ ወይንም መስፈርት ሲመረመር ህወሓት ምንም ወዳጅ የለውም። ሊኖረውም አይችልም። ከጅምሩ የተመሰረተበትን ሰነድ ቀረብ ብለን ብናየው፤ ***ዐማራውን ዋና ጠላቴ ነው ብሎ ፈርዶበታል።*** *"የመሬት ነጠቃው ተደጋጋሚነት ድህነትን፤ የእርስ በርስ ግጭትን ፈጥሯል፤ አጠናክሯል። አሁንም እንደ ዱሮው፤ ህወሓት ኢትዮጵያን አፈራርሼ ወደ ክልሌ ምሽግ እገባለሁ" ያለና የሚል ቡድን ነው። ታላቋን ትግራይ እመሰርታለሁ ያለ ቡድን ነው። የኢትዮጵያን መሬት ለሱዳን የሰጠ ቡድን ነው። አንቀጽ ሰላሳ ዘጠኝን በሕገ መንግሥቱ ያጸደቀው ለፍትህ፤ ለዲሞክራሲ፤ ራስን በራስ ለማስተዳደር መብት አይደለም። ቢሆን ኖሮ ይደገፋል።* ምክንያቱም፤ ስልጣኑና መብቱ የሕዝብ ይሆናል። ህወሓት አንቀጽ ሰላሳ ዘጠኝን መሳሪያ ወይንም በትር አድርጎታል። ዋናው ምክንያት ለጭቁኖች ነጻነት አስቦ አይደለም። **ዋናው ምክንያት ከፋፍሎ ለመግዛት** ስለሚያስችል ነው። "እኔ ካልገዛሁ ኢትዮጵያ ትፈራርሳለች" ለሚለው የጠባብ ብሄርተኞች ሴራ በትር ሆኖ እንዲያገለግል ነው። አገርን እያስፈራራ የሚገዛ ቡድን የትም ታይቶ አይታወቅም። አገር የምትሸጥ፤ የምትለወጥ፤ የሚነገድባት የሆነችው በዚህ ቡድን የበላይነት ዘመን ነው።

በሌላ አነጋገር፤ አንቀጽ ሰላሳ ዘጠኝ በሕገ መንግሥቱ ከፍተኛ ቦታ የያዘበት ምክንያት፤ ለህወሓትና ለሌሎች ለተገንጣዮች ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ነው። ይህ አንቀጽ በማንም ሃላፊነት በሚሰማው መንግሥት የማይታሰብና የማይደረግ መሆኑን ታዛቢዎች ያውቁታል። "እኔ በበላይ ሆኘ ካልገዛሁ፤ እኔ በበላይ ሆኘ ድርጅታዊ ምዝበራ ለማካሄድ ካልቻልኩ" ኢትዮጵያ ብትፈራርስ ደንታ የለኝም የሚል አገዛዝ መስርቶ፤ ሌሎች እንዲቀበሉት የሚሞክር፤ በታሪክ የመጀመሪያውን ደረጃ የያዘው ህወሓት ነው። እንዲህ ባለ ሁኔታ አገርና ሕዝብ ኃብታም ሊሆን አይችልም። ድህነት ሊጠፋ አይችልም። እድገት ሚዛናዊ ሊሆን አይችልም። ምክንያቱም፤ የምርት ኃይሎች አያድጉም፤ አይስፋፉም፤ የስራ እድል በሚፈለገው መጠን አይፈጠርም። የገበያ ትሥስር አይኖርም። እያንዳንዱ ክልል የተለየ አገር የሆነበት ሁኔታን ፈጥሯል። ስለሆነም፤ ፍትሃዊ የሆነ የእድገት ውጤት ስርጭት አይታሰብም። ካፒታል በገፍ ይሰረቃል፤ ይባክናል። ባለሥልጣናት የዲፕሎማቲክ ፓስፖርት ተጠቅመው የውጭ ምንዛሬ ከአገር ያሸሻሉ፤ ያሸሹት አልበቃቸውም። "እኔ ብቻ" ማለት አብዛኛውን ኃብትና ጥሪት መያዝ መብቴ ነው ማለት ነው። ይህ ሲሆን፤ **Concentration of capital and restrictions on** competition is inevitable (EFFORT, MIDROC etc). ካፒታል በጥቂቶች እጅ ሲያዝ የሚያስከትለው የማህበረሰብ ውድመት ቀላል አለመሆኑን ባለፉት አስራ ሁለት ወራቶች በግልጽ አይተናል። ወጣቱ ትውልድ የሚሰጠው መልእክት እኮ "እድገቱ ለእኔ ፋይዳ የለውም" የሚል ነው። ሁኔታው እንዳለ ከቀጠለ የኢኮኖሚው እንቅስቃሴ ይቆማል፤ ኢንቬስትመንት ይቆማል፤ ብዙ ኩባንያዎች ይከሰራሉ። ኃብት ያለው ኃብቱን ያሸሻል።

የህወሓቶች ጠባብ ብሄርተኛ የፖለቲካና የኢኮኖሚ የበላይነት በበለጠ የሚጎዳው ለመወዳደር፤ ለመፍጠር፤ ለማምረት፤ ለመግዛትና ለመሸጥ የሚፈልገውን ወጣት ትውልድና በአገር ቤት እየሰራ የሚጣጣረውን ግለሰብና ቤተሰብ ነው። ይህ የበላይነት አገር አቀፍ ኃብታም እንዳይፈጠር አድርጎታል። ምክንያቱም፤ የህወሓት አባል ወይንም ብሄር አካል ያልሆነ ሁሉ ወደ ገበያው ለመግባት ትልቅ አጥር መዝለል አለበት፤ የጠባብ ብሄርተኞች አጥር። 102 ሚሊየን ሕዝብ አጥር ዝለል (ታማኝ ሁን፤ ጉርሻ ስጥ ወዘተርፈ) ከተባለ በአገሩ ሰርቶ ኃብታም ለመሆን አይችልም። ሁሉም ሊሰደድ አይችልም፤ **የሚቀበለው አገር አያገኝም። ያለው አማራጭ ስርዓቱን መለወጥ ነው።** ወጣቱ ትውልድ የሚያካሂደው ትግል ይህን ያንጸባርቃል።

**የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ መዋቅር** ሊለወጥ የማይችለው በየቦታው የህወሓቶች አጥር ስላለ ነው። የመመሪያ አጥር፤ የግብ አጥር፤ የብድር እጥረት አጥር፤ የመሬት ይዞታ አጥር ወዘተርፈ። ሕዝብን በቋንቋና በብሄር መለያየት አጥሩን ያጠናክረዋል። የካፒታል፤ የገበያና የእውቀት እንቅስቃሴው ታጥሯል። የሕግ የበላይነት አይታሰብም። ግልጽነት አይታሰብም። አግባብ ያለው መረጃ አይታሰብም። የማህበረሰብ ግንኙነት ታጥሯል። ሕዝብ የአገሩን ታሪክ እንዳያውቅ አጥር ተገንብቶበታል። እነዚህ አጥሮች ሕዝብ የጋራ ችግሮቹን በጋራ እንዳይፈታ ጫና ሆኖባቸዋል። የአጥሩን መሰናክል ቀረብ ብለን ብናየው፤ ህወሓቶች ያደረጉት ተንኮል፤ ሁሉም ለብሄሩ፤ ሁሉም ለክልሉ፤ ሁሉም ለመንደሩ የሚለው መርህ ይስበዋል። ችግሮች በያካባቢው መፈታት እንዳለባቸው አልክድም። የራሱን ችግር የሚያውቀው ነዋሪው ነው። ሆኖም፤ በጋራ የሚፈቱ ብሄራዊ ችግሮች በመንደር ሊፈቱ አይችሉም። ብሄራዊ ችግር ብሄራዊ መልስ ያስፈልገዋል። የቲቤት ማህበረሰባዊ፤ ኢኮኖሚያዊ፤ መሰረተ-ልማታዊ ችግሮች የተፈቱት በመላው የቻይና ሕዝብ ጥርት ነው። የትግራይ መሰረተ ልማት ሊሻሻል የቻለው ህወሓቶች ከሌላው ኢትዮጵያ በማረኩት የገንዘብ/ባጀት አቅም ነው።

### የማህበረሰባዊ ካፒታል ናዳ (መናድ)

ያለፉት ሃያ አምስት ዓመታት ያስተማረን አንድ አፍራሽ ሂደት ወጣቱ ትውልድ የአገሩን ታሪክ እንዳያውቅና በቋንቋና በጎሳ የተመሰረተ አዲስ ታሪክ እንዲማርና ይህን ሰው ሰራሽ ታሪክ እንዲቀበል መገደዱ ነው። በደርግ ዘመን አስር ዓመት የነበረ ወጣት፤ አሁን ከሰላሳ አምስት በላይ የሆነው እና በህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ ተወልዶ ያደገው **ከሕዝቡ ሰባ በመቶ** በላይ ይሆናል። ይህ ወጣት ትውልድ የአገሩን ታሪክ እንዳያውቅ፤ በምትኩ የራሱን ብሄር ታሪክ የበላይ አድርጎ እንዲቀበል

ተደርጓል። ይህ **የብሄር ካርድ** የጠቀመው ህወሓቶችንና የእነሱን አጋሮች ነው። የራስን ብሄር ታሪክ ማወቅ የሚደገፍ ነው። ችግሩን ግን ልንከድ አንችልም። ዘጠኝ ክልሎችና ተጨማሪ ብዙ ንኡስ ክልሎች ተመስርተው (ራያና አዘቦ፤ ቅማንት ወዘተርፈ) ኢትዮጵያ የሚባለው ሰብሳቢና የጋራ እሴት በአማራ፤ በትግራይ፤ በደቡብ፤ በኦሮሞ ወዘተርፈ የማንነት ተቀዳሚነት እሴት ተለውጧል። "እኔ ኢትዮጵያዊ ነኝ" ማለቱ ነውር ሆኖ፤ "እኔ አማራ፤ ትግሬ፤ ኦሮሞ ወዘተርፈ ነኝ" ማለት እየተመረጠ ነው። ይህን የሚፈልገው ገዢው ፓርቲ፤ በተለይ ህወሓት ነው። ይህ ለማን ይጠቅማል፤ ለማን መሳሪያ ሆኖ አገልግሏል? መልሱን እያንዳንዱ ዜጋ መመለስ አለበት። የማይካደው ግን፤ የመጀመሪያውና ዋናው ተጠቃሚ በከፋፍለህ ግዛው የፖለቲክና የኢኮኖሚ የበላይነቱን የያዘው ህወሓት ነው። ሌላው የፖለቲካ ነጋዴዎች ናቸው፤ ነገ ስልጣን እንይዛለን ብለው የሚታገሉት። ህወሓቶች ወጣቱን ትውልድ ለሞት፤ ለድህነትና ለስደት ዳርገው "ማንነትክን እናከብራለን" ይላሉ። "ሕገ መንግሥቱን አክብር" ይላሉ። ይህን ሊመልሰው የሚችለው ወጣቱ ትውልድ ነው። የብሄርና የኃይማኖት ከፋፋዮችን አልቀበልም የሚል መርህ ተከትሎ። ለራሱ ሲል!

አንዱ አስከፊ ውጤት ሰፊው ትውልድ የሚቆራኝበት፤ እርስ በርስ የሚወያይበት የጋራ  ወይንም **ብሄራዊ ዓላማና የጋራ የእሴቶች ቋንቋ (Shared Knowledge)** እንዳይኖር መደረጉ ነው። የኢትዮጵያ ወጣት ትውልድ ከጎረቤቱ ከኬንያ ወጣት ትውልድ ሊማር ይችላል። የኬንያ ኢኮኖሚ ስፋት አለው፤ የኬንያ ሕገ መንግሥት በብሄር ልዩነቶች አይመራም፤ መገንጠልን አይቀበልም። የግል ክፍሉ እየተስፋፋ ነው። ሁሉም በሞያውና በካፒታሉ የሚሳተፍበት ገበያ አለ፤ ስቶክ ማርኬት አለ። ኢኮኖሚው እየተስፋፋ ሲሄድ የብሄር ልዩነቶችም ከእርስ በርስ ግጭት ወደ እርቅ፤ ሰላምና አብሮ መኖር ያመራሉ። ኪኩዩ ነኝ ከማለት ኬንያዊ ነኝ ማለትን ይመርጣሉ። ጋናም የሆነው ተመሳሳይ ነው፤ ናይጀሪያም እያደገ የሄደው በመቻቻልና በመደጋገፍ ነው። በልዩነትና በብሄር አድልዎ ያልተበከለ ኢኮኖሚ ለሁሉም እድል ይከፍታል። አብዛኛው ሕዝብ ከድህነት ነጻ የሚሆነው አገዛዙ አመቻችና አጎልማሽ ሲሆን ነው። የግሉ ክፍል አስተማማኝ ሲሆን ነው።

አንዳንድ ግለሰቦች ኢትዮጵያ "የለችም" የሚሉት በዚህ ህወሓቶችና አጋሮቻቸው በፈጠሩት የብሄር ልዩነቶችና በጸረ-ኢትዮጵዊነት አቋማቸው ምክንያት ነው። ይህ የተሳሳተ አስተሳሰብ ወደሌሎች ጉዳዮችም ተዛምቷል። ለምሳሌ ነጻነትና ፍትህ ሲባል የጋራ መሆኑ አጠያያቂ እየሆነ መሄዱ ከዚህ ብዝሯታ ጋር የተያያዘ ነው። ለዚህ የጋርዮሽ እሴቶች አለመኖር ሰለባው ወጣቱ ትቅውልድ ሆኗል። በአገሩ ተንቀሳቅሶና ሰርቶ ለመኖር የሚፈልገው ኢትዮጵያዊ ሁሉ እየተጎዳ ነው።  በአሁን ስርዓት ይህ ሁሉን አቀፍ የሆነ የግል ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ አይቻልም። "እድገቱ ለአንተ ዝግ ነው" ይባላል። ይህ የክልላዊነት ውጤት ነው። የፖለቲካ ልሂቃን የጋራ ዐላማ ስለሌላቸው ብዝሯታውን አባብሰውታል። ዝጉን ገበያ አባብሰውታል። ህወሓቶች በማንኛውም ዘርፍ ተወዳዳሪ ትውልድ አይወዱም፤ ተወዳዳሪ ጠላታቸውና ኢላማቸው ነው። ህወሓት **ወጣቱን ትውልድ ነጥሎ ለመምታት አመች** ሁኔታዎችን የፈጠረላቸውም ይኼው ተወዳዳሪና ለውጥ ፈላጊን መጥላቱ ነው። መሪ እንዲፈጠር፤ ከተፈጠረ በህይወት እንዲኖር አይፈቅድም።  የሃሰትና የበደል ፖለቲካ ፋብሪካው ሃያ አራት ሰአት ይሰራል። ህወሓት "እድገት አለ፤ የእድገት ጠላት አትሁን" ይላል። ህወሓቶች "ተሃድሶ፤ ተሃድሶ" ሲሉ ምንድን ነው የሚታደሰው ብለን ብንጠይቅ፤ ራስን መጥቀም ብቻ ነው "ተሃድሶው" የሚል የማያሻማ መልስ እናገኛለን። ሕዝብን አፍኖ፤ ወጣቱን እየገደሉና እያሰሩ "ተሃድሶ" ምን ትርጉም አለው? ህወሓት የፈጠራ ታሪክ ተጠቅሞ የዐማራውን ለም መሬት ወደ ታላቋ ትግራይ አጠቃሏል፤ የወልቃይት ጠገዴ ጥያቄ የማይፈታው ለዚህ ነው።

አስደናቂውና አከራካሪው፤ ይህን የውሸት ፋብሪካ የሚሰራው ህወሓት ብቻ አይደለም። ለአንዳንድ ግለሰቦችና ቡድኖች የሌለ ታሪክ፤ በመሬት የሌለ ሁኔታ ፈጥሮ መከራከር አንዱ የፖለቲካ ጨዋታ ሆኗል። ገዢዎች ቢዋሹ አይፈረድባቸውም፤ ጥቅም ስለሚያገኙበት፤ ዓለምን ለማባበል ስለሚያስችላቸው። ፍትህ እንፈልጋለን የምንለው በምንሰጣቸው ምሳሌዎች ለምን እንዋሻለን? ለምን ግልጽ የሆነ አቋም የለንም? ለምሳሌ፤ ፍትህ ይኑር ወይንም ዲሞክራሳዊ መብት ይከበር ካልን ማንንም ብሄር ወይንም ግለሰብ መለየት የለብንም፤ ሁሉን አቀፍ መሆን አለብን። ፍትህ የምንመኝ ማንንም ብሄር ወይንም ኃይማኖት አንጠላም። ጠባብ ብሄርተኝነት፤ የብሄር ትእቢተኛነት፤ ጥላቻና ፍትህ አብረው አይሄዱም፤ ውሸትና የሕግ የበላይነት አብረው አይሄዱም። የሁሉም መብቶች ይከበሩ! የአንዱ ህይወት ከሌላው ህይወት አይለይም ወይንም አይበልጥም ለማለት መድፈር አለብን። **ግልጽነት ካለ የዝግ ችሎት አስፈላጊ አይሆንም። የዝግ ችሎትን ልምድ ያደረገው ትግራይን የከለለው ወይንም ያጠረው ህወሓት ይበቃል። የዝግ ችሎት የሚፈጥረውና የሚያጠናክረው ህወሓት የፈጠረውን የክልል (የመለያየት) ስርዓትን ነው።** ያጠናከረው የፈጠረውን የአንድ አናሳ ብሄር የፖለቲካና የኢኮኖሚ የበላይነትን ነው። ይህ ከቀጠለ ወጣቱ ትውልድ ያለው አማራጭ ለራሱ መብቶች መታገል ወይንም መሰደድ ነው። ህወሓት አስፈላጊ ነው ተብሎ የሚገመተውን **በዓመት 2.4 ሚሊየን የስራ እድል** ሊፈጥር አይችልም። ቢቻል ኖሮ እስካሁን ያደርገው ነበር። ኢኮኖሚው አሳታፊ ከሆነ፤ የግል ክፍሉ ከተስፋፋ ከዚያም በላይ የስራ እድል ለመፍጠር ይቻላል።  በማንኛውውም **ዓለም ዘጠና በመቶ** የሚሆነውን የስራ እድል የሚፈጥረው የግሉ ክፍል ነው። የግል ክፍል ስል፤ በሁሉም ኢትዮጵያ የሚሰራው የግል ክፍል ተሳትፎና መስፋፋት ማለቴ ነው። የመሬት ይዞታ ቢሻሻል፤ የገጠሩ ኢኰኖሚ ዘመናዊ እየሆነ ይሄዳል፤ ያ ብዙ ሚሊየን የስራ እድሎች

ይፈጥራል። የገጠሩ ሕዝብ ኃብታም ይሆናል። ዝግ ኢኮኖሚ፤ በጥቂቶች የተያዘ ሞኖፖሊ ተብሎ የሚጠራ ኢኮኖሚ ይህን ለማድረግ አይችልም፤ መቶ ዓመትም ቢቆይ መሰረታዊና ፍትሃዊ የኢኮኖሚ ለውጥ መፍጠር አይችልም።

**ህወሓቶችና ደጋፊዎቻቸው ሃቁን መቀበል አይችሉም**

ያም ሆነ ይህ፤ ሃቁን መቀበል የተሳነው የህወሓቶች አገዛዝ ወጣቱ ትውልድ አሰቃቂና አጥፊ በሆነው ስርዓት ምክንያት ወደሚከተለው ድምዳሜ መድረሱን ይክዳል፤ ባይክድም አይቀበልም። ለወጣቱ ትውልድ ያሉት አማራጮች የተወሰኑ ናቸው። ለመሆኑ ምንድን ናቸው?

አንድ፤ ያለውን አስከፊ ስርዓት ተቀብሎ መከራዎችን መሸከም ነው። ይህ የማይታሰብ ሆኗል፤ ወጣቱ ትውልድ ከዚህ የጨለማ አስተሳሰብ ራሱን ነጻ አውጥቷል። ከዚህ የበለጠ ጭካኔ ሊደርስብኝ አይችልም ብሎ ወስኖ የፍርሃትን ድባብ ሰብሮታል። ለመብቱ፤ ለነጻነቱ እና ለአገሩ መስዋእት እየሆነ ነው። በጎንደር የሚካሄደውን ትግል ሳይ፤ ይህ ክፍል "የአፍሪካ አፍጋኒስታን" የሚሆንበት ሁኔታ እየተፈጠረ ነው፤ ይህን የሚያስብሉ ሁኔታዎች ይታያሉ። ወጣት፤ ሴት፤ አባት፤ እናት መንፈሳዊ መሪ፤ ገበሬ፤ ከተሜ ወዘተርፈ ሳይለይ ሁሉም "ከእንግዲህ አንገደልም፤ ከእንግዲህ አንደፈራም፤ ከእንግዲህ በመሬታችን ላይ አንደራደርም" የሚል ይመስላል። ትግሉ አንዱ ቦታ ጋብ ሲል ሌላው ይነሳል። ጀግናና ጀግንነት እየተፈጠረ ነው፤ አዲስ አመራር እየተፈጠረ ነው። ታሪክ የለህም፤ ማንነትህን አንቀበለም የተባለው፤ ማንነቱን ተቀብሎ ታሪክ እየፈጠረ ነው፤ ኢትዮጵያ እንዳትጠፋ እየሞተላት ነው። ሌላው ኢትዮጵያዊና እኛ ከዚህ ወጣትና ደፋር ትውልድ ልንማር እንችላለን። እኛም በጊዜአችን ደፋርና አገር ወዳድ፤ ሁሉንም ሕዝብ ወዳድ ነበርን ብለን ድጋፍ እንስጠው። የድርጅት አምልኮን ሸክም ከትክሻችን እናውርደው። አንከፋፈልም ብለን እንነሳ! የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲተባበር አምባሳደር እንሁን!!

ሁለት፤ ህወሓት ከአለፉት አስራ ሁለት ወራቶች የሕዝብ አመጽ ተምሮ የፖለቲካ ውይይት፤ ድርድርና የስልጣን ሽግግር ለማድረግ ፈቃደኛ እንዲሆን ማስገደድ ነው፤ በራሱ ፈቃድ ለድርድር አይቀርብም፤ እብሪተኛና ትእቢተኛ ነው፤

ላወቀበት፤ ይህ አማራጭ የሚከፈለውን የኢኮኖሚ፤ የተፈጥሮ ኃብት፤ የሰው ህይወት እልቂት፤ ያለመረጋጋት ወዘተርፈ ዋጋ ይቀንሳል፤ ሆኖም፤ ህወሓት አያውቅበትም፤ መልሱ ግድያና አፈና ነው፤

ይህ አማራጭ ተግባራዊ ቢሆን፤ አገሪቱ አስተዋይና ለአገርና ለሕዝብ ደህንነት የሚቆረቆሩ አባላት፤ አባቶችና መሪዎች እንዳሏት ያሳያል፤ የዓለም ሕዝብ ያከብረናል፤ አማራጭ እንዳለ አስተማማኝ ሁኔታዎችን ይፈጥራል። ህወሓቶች እነ ፕሮፌሰር መረራን ሲያስሩ ለአገር ተቆርቋሪዎችን አሰሩ ማለት ነው፤

የኢትዮጵያ የውጭ ጠላቶች መግቢያ ቀዳዳ እንዳይኖራቸው ያመቻቻል፤ ህወሓቶች ለውጭ ጠላቶች ወንፊቶች እየሰሩ ነው፤

የተገለለውን ብዙሃን ለማሳተፍ ከቻለች፤ አገሪቱ በገጠማት የኋላ ቀርነት፤ የድህነት፤ የስደት፤ የሙስናና ሌሎች ጠንቆች ላይ እንድታተኩር ያመቻቻል፤ ኢትዮጵያ ኃብታም ትሆናለች፤ ጠንካራ ትሆናለች፤ ራሷን ታስከብራለች። ህወሓቶች ራሳቸውን ብቻ ለማገልገል ስለፈለጉ ተሳትፎን አይደግፉም፤

የኢትዮጵያ ዘላቂነት ይጠናከራል፤ በውጭ ኃይሎች ላይ ያለው ጥገኝነት ይቀንሳል ወዘተርፈ። ህወሓቶች የኢትዮጵያን ዘላቂነት ቢፈልጉ አደጋዎችን ለመቋቋም የፖለቲካ በሩን ይከፍቱ ነበር፤ አልከፈቱም፤ አይከፍቱም፤

ከሌሎች አማራጮች ጋር ሲነጻጸር፤ ይህ አማራጭ ይመረጣል የሚል እምነት አለኝ። ላወቀበት ማለቴ ነው። ግን ገዢዎቹም እኛም፤ አላወቅንበትም። ሌላው ቀርቶ ለመወያየት አልቻልንም።

ሶስት፤ ሌላው አማራጭ የትጥቅ ትግሉን አገር አቀፍ ማድረግ ነው። ይህ አማራጭ ሁሉም አፈናና ግድያ የደረሰበት የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲሳተፍ ያስገድዳል። ይህ ከሆነ፤ ማለትም፤ ለውጥ በትጥቅ ትግል ብቻ ከተባለ <u>**የሚከፈለው ዋጋ ከሌሎች አማራጮች የሚብስ ይሆናል።**</u> ኃብት፤ ቤት፤ መሰረተ ልማት፤ ኢንቬስትመንት ይወድማል፤ የሰው ህይወት በባሰ ሁኔታ ይጠፋል። አገር ይፈርሳል።

የህወሓት/ኢህአዴግ ገዢ ቡድን የመጀመሪያውን አማራጭ፤ "የእኔን አገዛዝ ተቀብለህ ኑር እንጅ" ሌላ አማራጭ አልቀበልም ካለ፤ ሁለተኛው አማራጭ፤ ማለትም፤ የሕዝብ አመጽ እየተስፋፋ መሄዱ አይቀርም። ይህንንም አማራጭ በተከታታይ አልቀበልም ብሎ የአስቸኳይ አዋጁን ተጠቅሞ ብዙ ሕዝብ ከጨፈጨፈ ሁኔታው ተባብሶ ወደ የእርስ በርስ ጦርነት፤ ማለትም ወደ ሶስተኛው አማራጭ የሚሸጋገር መሆኑ አይቀርም። ይህ አማራጭ በጣም አደገኛና ብዙ ዋጋ የሚከፈልበት ይሆናል። ኢትዮጵያ ሶሪያን ልትሆን ትችላለች።

### የህወሓቶች ኃይልን ማምለክ አደገኛ ነው

ህወሓት የሚመካበት ኃይል አገር አቀፍና ተከታታይ የሆነን ሕዝባዊ አመጽና ራሱን አደራጅቶ በመሳሪያ ለመታገል የቆረጠን የተባበረ ኃይል ሊቋቋመው አይችልም። ሆኖም፤ የብዙ ንጹህ ኢትዮጵያዊያን ህይወት እንደሚያልፍ መገመት ይቻላል። የእርስ በርስ ጦርነት ከተጀመረ፤ የውጭ መንግሥታት የሚሰጡትን እርዳታ ያቆማሉ የሚል ግምት አለኝ። ኢንቬስትመንት ያቆማል፤ አሁንም እያቆመ ነው። ሁኔታውን የሚያባብሰው የኢትዮጵያ ነባር ጠላቶችና ተገንጣዮች በአገር ቤት ያለውን መናጋት ለራሳቸው ጥቅም ለማዋል መቻላቸው ጭምር ነው። ሳውዲዎች፤ ካታሮች፤ ግብጾች፤ አክራሪዎችን ይወዳሉ። ይደግፋሉ። ልዩ ልዩ የውስጥ ጥናቶችና ዘገባዎች የሚያሳዩት፤ የኃይማኖት አክራሪዎች፤ አመፀኞች ስር እየሰደዱ እንደሚሄዱ ነው። ተቻችሎ የሚኖረውንና ጨዋውን የኢትዮጵያን ሕዝብ እያመሱት ነው ለማለት እንችላለን። የውጭ ኃይሎች የአገር ውስጥና የውጭ **ተቀናቃዮች (ተቃዋሚ ስብስቦች) ኢትዮጵያን እንደ አገር ተቀብለው፤ መአከል አድርገው፤** ኢትዮጵያዊያን ለመታደግ በጋራ እንዳይሰሩ፤ ለጋራ እሴቶች አብረው እንዳይንቀሳቀሱ የተለያዩ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ። አሳሳቢ ሆኖ የሚታየው ህወሓቶች ከራሳቸው የትግል ሂደትና ኢላማ ካደረጉት ከደርግ የአገዛዝ ውድቀት ለመማር **አለመቻላቸው ነው። አገር ወዳድ የሆኑ የህወሓትም ሆነ በጠቅላላ የኢህአዴግ አባላት ይህን መሰረታዊ ችግርና የውጭ ጫና አጢነው የውስጥ አክራሪዎችን ደፍረው ለመቋቋም አልቻሉም። አሁን ግን፤ ኢትዮጵያንና መላውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ደህንነት መምረጥ አለባቸው።**

**ምርጫው አንድ ነው፤ ኢትዮጵያን ከአደጋ ማዳን፤ የሕዝቧን መብት ማክበር። በተመሳሳይ ተቃዋሚ ተብየው ባለፉት ወራት የተገኘውን የለውጥ እድል እንደ ገና እያባከነው መሄዱ አሳፋሪ ነው። ይህ እድልን የማባከን የፖለቲካ ባህል ለመቋቋም ካልቻልን ሁላችንም በታሪክ ተጠያቂ መሆናችን አይቀርም አላለሁ።** ቢያንስ ቢያንስ መስዋእት ለሆኑት ወገኖቻችንና ለወላጆቻቸው፤ ለዘመዶቻቸው ማሰብ ለሕሊናም ይበጃል። ማንም ኢትዮጵያዊ አያገባኝም የሚልበት ወቅት አልፏል።

### አገርን የማዳን ጥያቄ ጊዜ አይሰጥም

የህወሓቶች ሰላማዊ የሆነ፤ ሁሉን አሳታፊ የሆነ፤ **አገር አድን የሆነ፤** ሕዝብን፤ የትግራይን ሕዝብ ጭምሮ፤ ከእልቂትና ከጎሳ ጥላቻ አድን **የሆነ እና ሁሉን አሳታፊ ወደሚሆን ዲሞክራሳዊ ስርዓት የሚያመቻች ሽግግር ለመሄድ አንፈልግም የሚሉበት ዋና ምክንያት ፍርሃትና ራስን ማታለል** መሆኑ ይገባኛል። ግን፤ ያላሰቡት ሌላውን አጥፍቶ መጥፋትም ሊከሰት የሚችል መሆኑን ነው። ይገባኛል፤ ይኼ ሂደት ቀላል አይደለም፤ ፍርሃት ብቻ ከሆነ ሁላችንም ልናስብበት ይገባል።

አንድ፤ ህወሓቶች እኛ ስልጣን ከለቀቅን፤ ልክ በደርግ ውድቅት ማግሥት እንደሆነው፤ ሁላችንም በሕዝብ እልቂት፤ በምዝበራና ያለ አግባብ ኃብትን በማካበትና በማሸሽ፤ በማባከንና ሌላውን በማግለል ወንጀሎች እንከሰሳለን የሚል ግንዛቤና እምነት ያላቸው ይመስላል። ለዚህ የተቃዋሚው ክፍል አማራጮችን የማቅረብ ግዴታ አለበት። ውይይት የሚጠቅመው ለዚህ ነው።

ሁለት፤ በተመሳሳይ፤ ህወሓቶች “እኛ ስልጣን የያዝነው በኃይል ስለሆነ የምንለቀውም በኃይል ብቻ ነው” የሚለውን ጊዜ ያለፈበት መርህ መከተላቸው መቆም አለበት። ማንም ኢትዮጵያዊ ለእንሱ ግደሉ፤ ዝረፉ፤ አድልዎ አድርጉ፤ ገንዘብ አሽሹ፤ መሬት ንጠቁ ብሎ ስልጣን አልሰጣቸውም። ሕዝብ ሳይወክለው የሌላውን መሬት የሚነጥቅ ወንበዴ ነው። ወንበዴነትን የሚቀበል ኢትዮጵያዊ ጸረ-ፍትህ፤ ጸረ-ሰላም፤ ጸረ-ኢትዮጵያ፤ ጸረ-ሕዝብ ነው። የመንግሥት ስልጣንን ይዞ ምዝበራ ማካሄድ ከውንብድና አይለይም። ንጹሃንን የሚያስርና የሚገድል ወንበዴ ነው። አንድ አናሳ ቡድን ሁል ጊዜ እኔ ብቻ ልግዛ፤ መብቴት ነው፤ እኔ ብቻ ልብላና ኃብት ላካብት፤ ስልጣኔ ነው” ካለ የሚከተለው አደጋ ሁሉንም እንደሚያሳጣው የሚጠራጠር ተመልካች ያለ አይመስለኝም።

በደቡብ አፍሪካ ከአስር በመቶ የማይበልጡ ነጮች “እኛ ብቻ እንብላ፤ እኛ ብቻ እንገዛለን፤ መላው ደቡብ አፍሪካ የእኛ ብቻ መጠቀሚያና መኖሪያ ነው፤ ሌላው ተገዢ እኛ ገዢ መሆናችን ይቀጥላል፤ ሌላው ድሃ፤ እኛ ኃብታም” በሚል ቅዠት የብዙ ጥቁሮችን ህይወት አጥፍተው ነበር። ልክ ህወሓቶች እንደሚያደርጉት የስለላ፤ የፖሊስና የመከላከያ ኃይላቸውን ለጭካኔዎቻቸው መሳሪያ አድርገውት ነበር። ጥቁሩን በጥቁሩ ላይ እንዲነሳም ሞክረው ነበር። ሰርጎ ገቦችን በመላው ዓለም አሰራጭተው ነበር። የጥቁሮችን አገር ኃብት ተጠቅመው፤ ለዲፕሎማሲ ስራ በያመቱ ብዙ መቶ ሚልየን ዶላር ወጭ ያደርጉ ነበር። ለግድያ አመች የሆኑትን የአስቸኳይ ጊዜ አውጆች ዘላለማዊ አድርገው ነበር። እነዚህ አዋጆች የብዙ ጥቁሮች ህይወት እንዲጠፋ ረድተዋል። የሕዝብ መብት ሙሉ በሙሉ ተዳፍኖ ነበር። እስር ቤቶች ሞልተው ሌሎች እስር ቤቶች ይሰሩ ነበር። ህወሓቶች ከ130 በላይ እስር ቤቶች ስርተው ብዙ ሽህ ኢትዮጵያዊያንን አጉረውበታል። ብዙ ሽህ የሚሆኑ ወገኖቻችን በማይታወቁ እስር ቤቶች ይማቅቃሉ፤ ይገረፋሉ። ይህች ኢትዮጵያ የምታስታውሰኝ የአፓርታይዷን ደቡብ አፍሪካን

ነው።

አንድ ነጭ የደቡብ አፍሪካ ጉዳይ እንቅልፍ ስለነሳው፤ "እግዚዖ" እያለ፤ ቢጨንቀው "**Cry the Beloved Country"** የሚል አስደናቂ መጽሃፍ ጽፎ ያለውን አደጋ አሳይቶ ነበር። አለን ፔይተን እንዲህ ብሏል፤

"The tragedy is not that things are broken. ... (ልክ አሁን ሕግና መንግሥት የለም እንደሚባልባት ኢትዮጵያ፤ ገዢው ቡድን ማንንም ተቃዋሚ በማይምርባት አገር)

"But there is only one thing that has power completely, and this is love. ... (ከሁሉም በላይ የሚያገለግለው ከብሄርና ዘር በላይ ፍቅር ነው፤ መተሳሰብን፤ ደግነትን ነው)

"Cry, the beloved country, for the unborn child that's the inheritor of our fear." (የማፈቅርሽ አገሬ፤ የማለቅሰው (ማልቀስ ያለብን ገና ላልተወለዱት ተተኪዎች ነው)። እኛም ማሰብ ያለን ለዛሬው ትውልድ ብቻ ሳይሆን ለተተኪው ትውልድ ጭምር ነው።

የኢትዮጵያ ሁኔታ ከአፓርታይዷ ደቡብ አፍሪካ ይብሳል እንጅ አያንስም። የኢትዮጵያ ሁኔታ በደቡብ አፍሪካ ነጮች ጥቁሮችን ስለገደሉ የተለየ ሊሆን አይችልም። የጥቁር ጨካኝ ቡድን ጥቃት በአገራችን እየተካሄደ ነው። ወገኖቻችን በገፍ እየተገደሉ ነው፤ እየታፈኑና እንዲሰወሩ እየተደረገ ነው። በኢትዮጵያ ስርዓቱ ስለተንገዳገደ የአስቸኳ አዋጅ ታወጀ፤ ታውጆ ብዙ ሽህ ወጣቶች ታስረዋል፤ ብዙ ሺህ እንዲሰወሩ ተደርጓል፤ ብዙ ሽህ ተገድለዋል፤ አሁንም እየሞቱ ነው። ብዙ ሚሊየን እናቶች እያለቀሱ ነው። ኃብታም የነበረው እየደኸየ ነው። ኃብቱን ከአገር እያሸሸ ነው። መጨነቅ ያለብን ለአሁኑ ትውልድ ብቻ አይደለም። ፔይተን እንዳለው ማልቀስና ማሰብ ያለብን ለተከታታይ ትውልድ ኑሮና ህይወት መሻሻል ጭምር ነው። ለተከታታይ ትውልድ ለማሰብ የምንችለው ለአንድ አገር በጋራ ለመቆም ስንችል ብቻ ነው። የተቀነባበረ ብሄራዊ ትግል የሚያስፈልገው ለዚህ ነው።

እኛም ለአገራችን ለኢትዮጵያ የወደፊት እድል ማሰብና ማልቀስ አለብን ማለት ነው። ማሰብና ማልቀስ በቂ አይደለም። ከዚህ ባሻገር ለዚህች ታሪካዊ አገር በአንድ ላይ መቆምና በአንድነት መታገል አለብን እላለሁ። **የጋራ የሆነ ወይንም ብሄራዊ ዐላማና የሚያስተባብር መርህና መፈክር እንፍጠር እላለሁ።** አገራችንን የምናጣት በራሳችን ድክመት፤ በራሳችን አለመስማማት፤ በራሳችን ድንቁርና፤ በራሳችን መከፋፈል ነው። ይህችን አገር አንዴ ካጣናት መልሰን እናቋቁማታላን የሚለው ብሂል ድንቁርና ነው። ህወሓቶች አመቻችተው እንደ ስጦታ ካቀረቡት ከኤርትራ መገንጠል እና የኢትዮጵያ የባህር በር ከመዘጋቱ ለመማር እንችላለን። ከዩጎስላቢያ መበታተን ለመማር እንችላለን። ከሶሪያ እልቂት ለመማር እንችላለን፤ ይህ በኢትዮጵያ አይሆንም ለማለት አንችልም፤ ሊሆን ይችላል።

ኢትዮጵያ "ፈጽሞ ትጥፋ" የሚለውም ብሂል ጠላቶች ከሚፈልጉት ምኞት፤ ከህወሓቶች የትግል ስልት ውጭ አይለይም። ኢትዮጵያ ትጥፋ ብሎ መናገር መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ተባብሮ የአድዋን ድል አልተጎናጸፈም፤፤ የጸረ-ፋሽስቱን ትግል፤ የሶማሌን ጦርነት፤ የኤርትራን ጦርነት፤ የባድሜን ጨምሮ፤ በጋራ አልተዋጋም፤ በጋራ መስዋእት አልሆነም እንደማለት ነው። ይህን የሚል ማንኛውም ግለሰብ ወይንም ቡድን ባርነትን ከነጻነት ይመርጣል ብል የተሳሳትኩ አይመስለኝም።

አግባብ የሚኖረው ክርክር ስርዓትን ለውጦ ፍትሃዊ በሆነ ስርዓት መተካት፤ ያለፉትን በደሎች በጽሞና ማየት፤ እንዳይደገሙ ማድረግ ነው። ልክ የደቡብ አፍሪካ ሕዝብ እንዳደረገው። የእርቅና ሰላም ውይይት የሚጠቅመው ከዚህ ላይ ነው። ህወሓቶች በዘርና በቋንቋ መለያየት የመሰረቱት ስርዓት የወለዳቸው ጠንቆች በቀላሉ አይፈቱም። የማይፈቱበት ዋና ምክንያት ሁሉም ወደ ብሄር ምሽጉ ስለገባና ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ችላ ስላላቸው ወይንም ፈጽሞ አልቀበልም ስላለ ነው። ይህ ከሆነ ኢትዮጵያ ለምትባለው አገርስ ማን ጠበቃ ይሁናት? ብለን ብንጠይቅ አጥጋቢ መልስ አናገኝም። ታሪካችንን ስለረሳነው ይሆን ወይንስ አዲስ ታሪክ ስለተጻፈ? አንዳንድ ግለሰቦች አዲስ ታሪክ ፈጥረው የተሳሳተ ድምዳሜ የሚያደርጉት ለዚህ ነው። ለምሳሌ፤ "ኢትዮጵያ የምትባል አገር የለችም" ያሉት የብሄር ምሁራን፤ ልሂቃንና ፓርቲዎች ናቸው። ኢትዮጵያ የምትባል አገር "ትፈራርስ" ወዘተ የሚሉት ብሂሎች ለሁሉም የብሄር አባላት ጉዳታቸው ቀላል አይደለም። ይህን የሚሉት ግለሰቦች ከዚህ ድምዳሜ ላይ የደረሱት ምን ጥናት አድርገው ነው? ማንን አማክረው ነው? የትኛውን ተራ ሕዝብ ጠይቀው ነው?" በገፍ መስዋእት የሆነውን ወጣት ትውልድ እንዴት ቢረሱት ነው?

አዲስ ሪፖርተር የጻፈው ትክክል ነው። የህወሓት/ኢህአዴግ መንግሥት ችግሮችን ለመፍታት የሚሞክረው "በአፈና፤ በግድያ፤ ወጣቱን በመሰወርና በማሰቃየት፤ በሃሰት ፕሮፓጋንዳ ነው"። ይህ ሕዝብን በኃይል የመቆጣጠር ስልት ብዙ **የመንግሥት ወጭ ይጠይቃል።** ሳያመርቱ ወጭን መጨመር ደሞ የኑሮ ውድነት ከቁጥጥር ውጭ እንዲሆን አድርጎታል።

ገዢው ፓርቲ ገቢ ሳይኖረው ገንዘብ ወደሚያትምበት፤ ብድር ወደሚጨምርበት ደረጃ ደርሷል። ሕዝባዊው እንቅስቃሴ ወደ ዐመጽ እንዲለወጥ እየሆነ ነው። ይህን የሕዝብ ዐመጽ የፈጠረው ስርዓቱ ነው፤ ሰላማዊ የሆነው ሕዝብ አይደለም። ሕዝብ የሚፈልገው ሙብቱን የሚያከብርለት መንግሥት ነው፤ የሚዋሽና የሚቀጣ፤ የሚያፍንና የሚያሳድድ መንግሥት አይደለም።

ሪፖርተር እንዳለው "ከመንግሥት ተቀጽላነት የወጣ ነፃ የሕዝብ እንቅስቃሴን በቀሰፈ አጠቃላይ የሙብቶች አፈና ውስጥ ከሌሎች የነፃነት ብሶቶች ይበልጥ አገራችን ውስጥ ቀድሞም፣ በጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ሞት አካባቢም፣ አሁንም ፊት ለፊት የሚወራጨው በሃይማኖቶች ውስጥ ባለው **<u>የመንግሥት ጣልቃ ገብነትና ጥልቅ ባይነት የተመረረው ብሶት</u>** ነው፡፡ ይህንን ብሶት **<u>በተለመደው የፀጥታ አፈናና</u>** «ከጥያቄዎች በስተጀርባ ፖለቲካዊ ዓላማ አለ»፣ «ሃይማኖትን ሽፋን አድርጐ አመፅ ለማነሳሳት ነው» ወይም «የአክራሪነት አደገኛ እንቅስቃሴ ነው» እያሉ ስም በመለጠፍና በማሰር መታገል፣ በኦርቶዶክስ ክርስትናም ሆነ በእስልምና የእምነት መሪዎች አመራረጥም ውስጥ እጅን በቀጥታም ሆነ በእጅ አዙር ሰዶ አቦካለሁ ቢባል ውጤቱ መመለሻ ላይኖረው ይችላል፡፡ ኃላፊነት የሚሰማውና አስተዋይ አዕምሮ ያለው አንድ የሆነ ግጭትና ግድያ ምን ያህል የጣጣ ሰበብ ሊሆን እንደሚችል፣ የንድ ብሶት ፍንዳታ **<u>ከሌሎች ብሶቾች ጋር ተላልሶ ሊያጥለቀልቅ</u>** እንደሚችል መመልከት አለበት።" መሰረታዊ ችግሮችን ለመፍታት በመሞከር ፋንታ በሁሉም የማህበራዊ ኑሮ፤ በሁሉም የአስተዳደር ሁኔታ፤ በሁሉም የፖለቲካ ዘርፎች የሚካሄደው ጫናና አፈና የኢትዮጵያን ሁኔታ አባብሶታል." (The regime is compounding the problem by intensifying repression and oppression instead of opening-up political, social, economic and political space). Its response to the root causes of the Ethiopian crisis is a recipe for disaster."

በተቃዋሚው ክፍልም ያለው ትግልና አማራጭ ለመሰረታዊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ችግሮች ተመጣጣኝ አይደለም፤ ተመጣጣኝ አማራጭ አልሰጠም። ሕዝብ የሚጠይቀውን ወደ ጎን ትቶ በአቋራጭ የፖለቲካ ስልጣን ለመያዝ ወይንም የመገንጠል ዐላማን ስኬታማ ለማድረግ የሚደረግ ስልት ከህወሓት/ኢህአዴግ አመራር እንዴት ሊለይ ይችላል? የአንዳንዶቹ ቡድኖች፤ ስብስቦችና ግለሰቦች አስተሳሰብ ከጣሊያኖች፤ ከአረቦች፤ ከሻቢያዎችና ከህወሓቶት በምን ይለያል? ብለን ብንጠይቅ መልሱ ቀላል ነው። ለመለየት አስቸጋሪ ነው። አማራጮችን ሲሰጡ ማንንም አልጠየቁም፤ ከሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር አልተወያዩም። ወጣቱ ትውልድ የሚለውን ምንም አልሰሙም። ባጭሩ፤ የሚሰጡት አማራጭ የራሳቸው ምኞትና ፍላጎት ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ተጋብቷል፤ ተዋልዷል፤ ብዙ ሚሊየን ኢትዮጵያዊ የአንድ ብሄር አባል አይደለም። ድብልቅ ነው። በኢትዮጵያዊነቱ ያምናል። ሕዝብን የሚጋራው እሴት የለም ብሎ መደምደም የማይለያየውን ሕዝብ ለመለያየት የሚደረግ ተንኮል ነው። ይህ ከህወሓቶች አይለይም፤ እንዲያውም የእነሱ አጀንዳ ነው። እነዚህ በታታኝ ግለሰቦችና ከኋላቸው ያሉ የጠባብ ብሄርተኞችና የኃይማኖት አክራሪዎች ቡድኖች ትክክል ናቸው ብለን ከተቀበልን--እኔ አልቀበልም--ከህወሓቶችና **ከደጋፊዎቻቸው በብሄር ተደራጅተው ከሚገዙት ስርዓት አባላት በምን ይለያሉ? ትግሉ የስልጣን ነው ወይንስ ስርዓትን የመለወጥ? ብለን መጠየቅ ያለብን <u>በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት እምነት</u> ያለን ግለሰቦችና ስብስቦች ነን። ከዚህ ላይ ጨዋነት የለም፤ መኖርም የለበትም። ኢትዮጵያዊያን ብሄራዊ (አገር አቀፍ) እና መላውን ሕዝብ የሚወክል ትግል ማካሄድ አለብን።**

**ለማጠቃለል፤ በእኔ ግምትና እምነት በኢትዮጵያ ነጻነት፤ ዘላቂነት፤ ግዛታዊ አንድነትና ሉዐላዊነት ድርድር አይታሰብም።** በእኔ ግምት ሁላችንም የኢትዮጵያን መአከላዊነት እና የኢትዮጵያዊነትን የዜግነት መለያ ተቀብለን ሌሎችን ችግሮች ለመፍታት የምንችልበትን ሁኔታ ለማመቻቸት እድል ስላለን ይህ እድል አያምልጠን እላለሁ።

12/2/2016